2041

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን

# የ1982 የአንድ ዓመት

# የሥራ ክንውን ሪፖርት

አዲስ አበባ
ሐምሌ 1982

# ማውጫ

| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ .......................... | 1 |
| 2. የ1982 የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ ይዘት ..... | 2 |
| 3. የ1982 የአንድ ዓመት የሥራ ክንውን ግምገማ ... | 4 |
| 4. የበጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም ........... | 14 |
| 5. ያጋጠሙ ችግሮች .................... | 17 |

## የ1982 የአንድ ዓመት የሥራ ክንውን ሪፖርት

### 1. መግቢያ፤

የአገሪቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንባታን በተገቢው መንገድ ለማራመድና ለማፋጠን ተጨባጭ ሁኔታው በሚፈቅደው መሠረት ለአጭር ፣ የመካከለኛና፣ የረዥም ጊዜ ዕቅዶች ግብ እንዲመቱ ለማድረግ ማዕከላዊ ፕላንን እንደ ዓይነተኛ መሣሪያ ተወስዶ ሲሰራበት ቆይቷል::

ማዕከላዊ ፕላንን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ የፕላን መዋቅር በአገሪቱ በሰፊት መዘርጋት በየማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የፕላን አሠራር እንዲስፋፋና ልምዱም ደረጃ በደረጃ እየጎለበተ እንዲሄድ አመቺ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል:: ለኢኮኖሚና ማህበራዊ ፕላን ተግባራዊነት ደግሞ ስታቲስቲካዊ መረጃዎች በቅድሚያ በየዘርፉ መገኘት ወሳኝነት አለው:: በተለይም ለዕቅድ ዝግጅት፣ የልማት ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን ለመቀየስ፣ እንደዚሁም ምርምርንና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ለማከናወን በየክፍለተ ኢኮኖሚው ተጨባጩን ሁኔታ ሊገልጽ የሚችል ወቅታዊ ፣ የተሟላና አስተማማኝ የሆነ ስታቲስቲካዊ መረጃ ጠቃሚነቱ ከፍተኛ ወሳኝ እንደሆነ ይታመናል::

ስለሆነም የአገሪቱን የስታቲስቲክስ መረጃ ፍላጎት በማሟላት ረገድ የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ከፍተኛ ተግባርና ኃላፊነት የተጣለበት በመሆኑ ባለሥልጣኑ ለብሔራዊ ስታቲስቲክስ ሥራ ዕድገት አመቺ ሁኔታዎችን በመፍጠር ፣ በየጊዜው የተሻለ የአሠራር ዘዴዎችን በመቀየስ ተግባራዊ እንዲውሉ ጥረት በማድረግና እንዲሁም የአገሪቱን የዕድገት አቅጣጫና የአቅም ሁኔታዎችን በማገናዘብ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎችን የሚገልጹ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን ለማስገኘት የተቻለውን ሁሉ ሲያከናውን ቆይቷል:: አሁንም በማከናወን ላይ ይገኛል::

ባለሥልጣኑ ይህን የሚጠበቅበትን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችለውን ዕቅድና ፕሮግራም በማዘጋጀት ተግባር ላይ ያውላል:: በዚሁ መሠረት በ1982 ሊሰሩ የታቀዱ ሥራዎች ይዘትና በዕቅድ ዓመቱ ውስጥ የተከናወኑት ተግባራት በጥናቶች ዓይነት፣ የበጀትና የሰው ኃይል አጠቃቀም፣ በሥራው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደሩ ችግሮችም በዝርዝር ቀርቧል::

.../2

## 2. የ1982 የስታቲስቲክስ ሥራ ዕቅድ ይዘት፣

በ1982 ለማካሄድ የታቀደው የስታቲስቲክስ ሥራ በሦስት አበይት ይዘት ይኖሩታል፡፡ እነዚህም፣

2.1 የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ፣

2.2 ከተለያዩ ጥናቶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች አቀናብሮ በሪፖርት መልክ ማውጣትና፣ ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ሌሎች ሥራዎችን ማከናወን፣

2.3 በ1983 ይከናወናሉ ተብለው ለሚታሰቡ ጥናቶችና ሥራዎች አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግ ናቸው፡፡

### 2.1 የተለያዩ ጥናቶችን ማካሄድ በተመለከተ፣

በ1982 ስታቲስቲካዊ ጥናቶችን በማካሄድ ልዩ ልዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዕቅድ የተያዙት የጥናት ዓይነቶች ዝርዝር፡—

- የሰብል ትንበያ ጥናት፣
- የግብርና ቆጠራ፣
- ታላላቅ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎች፣ የማዕድንና ኤሌክትሪክ ጥናት፣
- የትራንስፖርትና መገናኛ ጥናት፣
- የዋጋዎች ጥናት፣
- የሕንጻዎችና የኮንስትራክሽን ጥናት፣
- የውሃ ሥራዎችን ሥርጭት ጥናት፣
- የሥነ ሕዝብ ጥናት፣
- ዝርዝር የቤተሰብና የልደት ጥናት ሲሆን አጠቃላይ የግብርና ቆጠራን በተመለከተ ግን አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት በአብዛኛው ቢጠናቀቅም በበጀት እጥረት ምክንያት ተሰርዟል፡፡ ሆኖም በየ ዓመቱ የሚካሄደው የግብርና ግምገማ ጥናት በዚሁ የፕላን ዓመትም በግል፣ በሕብረትና በመንግሥት እርሻ ባለይዞታዎች ላይ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

### 2.2 ከተለያዩ ጥናቶች የተሰበሰቡትን መረጃዎች አቀነባብሮ ውጤቱን በሪፖርት መልክ ማውጣትና ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ሌሎች ሥራዎች ማከናወን በተመለከተ፣

.. /3

3.1.1.6 የ1982 የአመራረት የሕብረት እርሻ ማህበራት ጥናት የመረጃዎች መሰብሰብ ተግባር በመከናወን ላይ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የእርሻ ሥራ አጠቃላይ ሁኔታ፣ የታረሰ መሬት ስፋት፣ የምርት መጠንና የቤት እንስሳት ብዛት የያዘ መረጃ ተጠናቆ ወደ ዋናው መ/ቤት የተላኩ ሲሆን የቀሪዎቹ መረጃ አሰባሰብ ተግባር ግን ወቅቱ ባለመድረሱ ቅጾቹ ተጠናቀው ያላመጡ እንዳሉ ታውቋል::

3.1.1.7 በገጠር የአምራችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናትን በተመለከተ በየጊዜው መረጃው የተሰበሰበ ሲሆን መጠይቆቹ ዋናው መ/ቤት ደርሰዋል::

3.1.1.8 ከዕርዳታ ማስተባበሪያና መቋቋሚያ ኮሚሽን ጋር በተደረገው ስምምነት መሠረት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች ወደ ኮሚሽኑ ተላልፏል::

3.1.1.9 በመስክ የመረጃ አሰባሰብ ሁኔታዎችን ለመቆጣጠርና ጥራቱንም ለመገምገም ከዋናው መ/ቤት የተውጣጡ ባለሙያዎችን ወደ ተለያዩ አስተዳደር አካባቢዎች በመላክ የቁጥጥርና የግምገማ ሥራ እንዲካሄድ ተደርጓል::

3.1.2 <u>በቋሚነት መረጃ የሚሰበሰብባቸው ጥናቶች፣</u>

3.1.2.1 <u>ዓመታዊ የማምረቻ ኢንዱስትሪዎችና የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ ጥናት፣</u>

የዚህ ጥናት የ1980 መረጃ አሰባሰብ ሥራ ተጠናቆ የ1981 መረጃ በመሰብሰብ ላይ ነው::

3.1.2.2 <u>ዓመታዊ የትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት፣</u>

ለትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት ዝግጅት የ1980 መረጃ በወቅቱ ተሰብስቦ ተጠናቋል:: የ1981 መረጃ ለመሰብሰብ መጠይቆች ተሰራጭተዋል::

3.1.2.3 <u>በከተሞች የዋጋዎች ጥናት፣</u>

በተመረጡ 23 ከተሞች /አዲስ አበባን ጨምሮ/ የሚካሄደው የዕቃዎችና የአገልግሎቶች የችርቻሮ ዋጋ ጥናት የመረጃ አሰባሰቡ ተግባር በየወሩ በመካሄድ ላይ ይገኛል::

../7

ዓመት መጀመሪያ ሪፖርቱን ለማውጣት ጥረት ይደረጋል። እን
ደዚሁም ለ1981 የኢንዱስትሪዎች መረጃ አሰባሰብ የሚያስ
ፈልገው የፋብሪካዎችን ዝርዝር የያዘ ዳሬክተሪና መጠይቆችን
አዘጋጅቶ በማሰራጨት የተሞሉ መጠይቆች በመሰብሰብ ላይ
ናቸው።

3.2.3 <u>ዓመታዊ የትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት፣</u>

ለ1980 የትራንስፖርትና መገናኛ መጽሔት ዝግጅት የተሰበ
ሰበው መረጃ የእርምትና የቅንብር ሥራው ተጠናቆ በመተየብ
ላይ ይገኛል።

3.2.4 <u>የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት፣</u>

3.2.4.1 የአዲስ አበባ የችርቻሮ ዋጋ መመዘኛ ኢንዴክስ ሥራ ወቅቱን
ጠብቆ በየወሩ እየተዘጋጀ ለተጠቃሚዎች እንዲሰራጭ ተደርጓል።

3.2.4.2 <u>በገጠር የአምራችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት፣</u>

በገጠር የአምራቾችና የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት ከሐምሌ እስከ
ግንቦት 1980 ያለው መረጃ የዳታ ኢንትሪና የኮምፒውተር ቅን
ብር ተጠናቆ የሪፖርት ዝግጅት ተጀምሯል። የ1981 መረጃ
የኢዲቲንግና ኮዲንግ ሥራ በሙሉ ሲጠናቀቅ የመጀመሪያው ሩብ
ዓመት የዳታ ኢንትሪ ሥራም ተጠናቋል። እንደዚሁም የ1982
የአንደኛና ሁለተኛ ሩብ ዓመት መረጃ የኢዲቲንግና ኮዲንግ
ሥራ ተጠናቋል።

3.2.4.3 የ1980/81 የ23 ከተሞች የችርቻሮ ዋጋዎች ጥናት ሪፖ
ርት ተዘጋጅቶ ለተጠቃሚዎች ተሰራጭቷል። እንደዚሁም የ1981/
82 መረጃ ደግሞ በኮምፒውተር የማቀነባበሩ ሥራ ተጠናቆ
ሪፖርቱን ለማውጣት በመተየብ ላይ ይገኛል።

../10

በቀን ሙያተኛነት ይቀጠራሉ፡፡ እንደዚሁም ለተወሰኑ ጥናቶችና ሥራዎች ጊዜያዊ የሥራ ውጥረት በሚኖርበት ወቅት ብቻ የጉልበት ሠራተኞች እንደሚቀጠሩ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

5. <u>ያጋጠሙ ችግሮች፡</u>

ባለፉት የዐቅድ ዓመታት በቀረቡት የዐቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ውስጥ መሥሪያ ቤቱን ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች መቅረባቸው አይዘነጋም፡፡ እነዚህ ችግሮች እስከዛሬ መፍትሔ ያላገኙ በመሆናቸው አሁንም በመሥሪያ ቤቱ ሥራ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ስለሆነም በዚህም ሪፖርት በተሰባሰበ ሁኔታ ዋና ዋናዎቹ ችግሮች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

5.1 <u>የቢሮ ጥበት፡</u>

የሀገርን እድገትና ልማት ለማፋጠን በማዕከላዊነት በየጊዜው የሚወጡትን እቅዶች ለማስፈጸም በሚደረገው የሥራ እንቅስቃሴ በብዛት እያደገ የመጣውን ሥራን የሰው ኃይል በተወሰኑ ቢሮዎችና የቦታ ይዞታ ለማስተናገድ ካለመቻሉም በላይ ሥራዎችን በሚፈለገው መንገድና ዓይነት ለማከናወን ከባድ ችግር እየፈጠረ ነው፡፡

ይህም የመሥሪያ ቤቱ ቋሚ ችግር ሆኖ የቆየው የቢሮ ጥበት ሁኔታ መፍትሔ እንዲያገኝ በ1980 የበጀት ዓመት ለሕንፃ ዲዛይን ሥራ በጀት ተፈቅዶ የመጨረሻ ደረጃ የዲዛይን ሥራ የተጠናቀቀ ቢሆንም በልዩ ልዩ ምክንያቶች የሕንፃው ሥራ በታሰበው ወቅት ባለመጀመሩ በአሁኑ ወቅት ችግሩ ተባብሶ ከባለሥልጣኑ አቅም በላይ ሆኗል፡፡

5.2 <u>የመሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ትብብር ማነስ፡</u>

ለስታቲስቲክስ መረጃዎች በወቅቱና በጥራት መገኘት የመሥሪያ ቤቶች፣ የድርጅቶችና የግለሰቦች ትብብር በከፍተኛ ደረጃ የሚጠበቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ባለፉት ዓመታት እንደታየው ሁሉ በዚህም የዐቅድ ዓመት የተሳትፎም ሆነ የትብብር ሁኔታ ዝቅተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህም ምክንያት ለሚዘጋጁት ልዩ ልዩ ስታቲስቲካዊ መጽሔቶች ይዘት መወሰንና መቀነስ እንደዚሁም ለሪፖርቶች መዘግየት አብይ ምክንያት ሆኗል ።

5.3 <u>የፋይናንስ አሠራር ሁኔታ ፤</u>

መንግሥት ለስታቲስቲክስ ሥራ ከፍተኛ ግምት በመስጠቱ ከ1973 ጀምሮ የካፒታል በጀት እየፈቀደ በየዓመቱ ሥራው በስፋት በመካሄድ ላይ መሆኑ የሚታወቅ ነው ። በአንጻሩም በየዓመቱ የሚፈቀደው በጀት በማደግ ላይ ይገኛል ።

በመሥሪያ ቤቱ አማካይነት የሚከናወኑት የስታቲስቲክስ ሥራዎች በየክፍለ ሀገር በመሆኑ ለደመወዝና ሥራ ማስኬጃ የሚውለው ገንዘብ በባንክ በኩል አዲስ አበባ ከሚገኘው ዋና መሥሪያ ቤት ይሰራጫል ። በተለያዩ ምክንያቶች በበጀት ዓመት መጨረሻ ከየክፍለ ሀገር የወጪ ማስረጃዎች ተጠቃለው ስለማይመጡና ስለማይወራረዱ መሥሪያ ቤቱ ሂሳቡን በወቅቱ እንዲዘጋ በገንዘብ ሚኒስቴር ይገደዳል ። በመሆኑም ለተከታዩ በጀት ዓመት ከወጪ ቀሪ የሚተላለፈው የሰነድ ሂሳብ ስለሚሆንና ሰነዶቹም በሚቀጥሉት ዓመታት ስለማይወገዱ መሥሪያ ቤቱ በፈሰስ ዕዳ ይጠየቅበታል ። የዕዳውም ክፍያ ተፈጻሚ የሚሆነው ከሚቀጥለው በጀት ዓመት በመቁረጥ ስለሆነ የዓመቱን ሥራ በሚገባ ለማንቀሳቀስ አስቸጋሪ ሆኗል ።

እስከ ዛሬ መሥሪያ ቤቱ በፈሰስ ዕዳነት ከሚጠየቅባቸው የሰነድ ሂሳብ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው ።

1ኛ. በ1973 በጀት ዘመን የመሥሪያ ቤቱ ረዳት ገንዘብ ያዥ የነበረው ግለሰብ ለክፍለሀገር ሥራ ማስኬጃ በባንክ በኩል ለመላክ ወጪ አድርጎት የነበረውን ገንዘብ ይዞ በመጥፋቱ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በየበጀት ዓመቱ እንደ አዲስ ዕዳ እየተቆጠረ በፈሰስ እንጠየቅበታለን ።

